# Learning by Ear 2013

**«መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ—«መዘዙን መቀበል»**

EPISODE 12: **«ህጉን ያላከበረ ዋጋውን ይከፍላል»**

**AUTHOR: James Muhando**

**EDITORS: Friederike Müller, ዳንኤልiel Pelz, Madelaine Meier**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**INTRO/OUTRO: NARRATOR**

**SCENE 1: AT BONGO ACADEMY**

- **በለጠ (M, 16)**
- **ዳንኤል (M, 16)**

**SCENE 2: AT THE POLICE STATION**

- **ፖሊስ ሙሉጌታ (M, 45)**
- **አቶ መኩሪያ (M, 45)**
- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**
- **3 OTHER INMATES (MALE, ADULTS)**

**SCENE 3: AT BONGO ACADEMY**

- **ርዕሰ መምህርት ሰብለ(F, 50)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **እየሩስ (F, 15)**
- **CROWD OF STUDENTS (5-8, MIXED GENDER)**

**SCENE 4: IN THE PRINCIPAL’S OFFICE**

- **ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)**

- ምህረት **(F, 15)**
- ንጉሴ **(M, 16)**
- ዳንኤል **(M, 16)**

**INTRO**

## 1. NARRATOR:

ጤና ይስጥልን! ይህ መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ–መዘዙን መቀበል” የሚለው ድራማ 12ኛ ክፍል ነው። በዚህ የሬዲዮ ድራማ የጥቂት አፍሪቃውያንታዳጊ ወጣቶችን የእለት ከለት ኑሮ እንመለከታለን። ሁሉም የከፍተኛው መደብ አባላት ልጆች የሚማሩበት የቦንጎ አካዳሚ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ነበሩ፤ ወይንም አሁንም ድረስ ናቸው ።– ሆኖም ርዕሰ መምህርቷ ለንጉሴ አባት ልጃቸው አደንዛዥ እፅ በመውሰድ በመጠርጠሩ ከትምህርት ቤት እንደታገደ ባለፈው ነግረዋቸዋል።:

***KW BEGIN***

## 2. EPISODE 11, LINES 118 – 119:

*ርዕሰ መምህርት ሰብለ: የትምህርት ቤታችን ጠባቂ ብዙ ጊዜ የትምህርት ቤቱ አጥር ስር ከተዋቂ እፅ ነጋዴ ጋ አይቶታል። እና ምናልባት ልጅዎ ማሪዋና ያጨሳል ብዬ እሰጋለሁ።*

***JUMBE:*** *ምን? የኛ ንጉሴ? (…)*

***KW END***

## 3. NARRATOR:

ምህረትበአዕምሮዋ ብዙ ነገሮች ይመላለሱባታል። አባቷ አቶ ሙላቱ አሁንም ላልፈፀሙት የስርቆት ወንጀል በፖሊስ ጣቢያ በቁጥጥር ስር ይገኛሉ።

## 4. EPISODE 7, LINES 104 – 105:

***SFX: BILLS BEING COUNTED AND HANDED OVER***

*አቶ መኩሪያ: ይሄውልህ ገንዘቡ። በል ሙላቱ አድሜ ልኩን ከእስር ቤት እንዳይወጣ አድርግልኝ። ማንም እንደማይደርስበት አድርጌ ከስርቆት ወንጀሉ ጋ አነካክቸዋለሁ።*

**5. NARRATOR:**

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከምህረት መንታ ወንድሞች አንዱ ብሩክ በጠና ታሟል። እህቱ ምህረት ወደ ሐኪም ቤትይዛው ስለሄደች ጠዋት ትምህርት አምልጧታል። ጓደኛዋ ትዕግስትም ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ምህረት አምና የነገረቻትን ምስጥር አውጥታለች።:

**6. EPISODE 11, LINES 58 – 67:**

*ትዕግስት: ርዕሰ መምህርት ሰብለ አንድ ነገር ልነግርዎ ፈልጌ ነበር። (…) **60.** ስለ ምህፈት ነው (…) **66.** (…)ኢይ! እንደዛ አይደለም… አርግዛለች*

*ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ምን?*

**7. NARRATOR:**

የህፃኑ አባት የምህረት የክፍል ልጅ ዳንኤል ነው። ሆኖም ዳኒ በአሁኑ ሰዓት ልቡ ሌላ ቦታ ያለ ይመስላል። «ህጉን ያላከበረ ዋጋውን ይከፍላል»የተሰኘውን የዛሬውን ጭውውት እንከታተል።

**<u>SCENE 1: AT BONGO ACADEMY</u>**

**8. SFX: SCHOOL ATMO, BREAKTIME, OUTSIDE**

**9. SFX: RUNNING FOOTSTEPS (በለጠ)**

**10. በለጠ:** **(pants)** እሺ ዳንኤል! እማገን ነው!

**11. SFX: FOOTSTEPS STOP**

**12. ዳንኤል:** ምንድነው በለጠ?

**13.** በለጠ: ይኼውልህ – ደብዳቤ መጥቶልሀል። ቴምብሩ ከላቦሪያ ነው። የዕጅ ፁሁፉ የሴት ልጅ ይመስላል። እህት እንዳለችህ አልነገርከኝም።

**14.** ዳንኤል: አሁን ደብዳቤውን ትሰጠኛለህ ወይንስ እንደፖሊስ ማውጣጣት ነው ስራህ?

**15.** በለጠ: **(laughs)** ኦ ኦ! ኧረ ይኼውልህ።

**16. SFX: LETTER EXCHANGED**

**17. SFX: LETTER RIPPED OPEN**

**18.** ዳንኤል: **(reads)** “የኔ ውድ ዳንኤል, …”

**19.** በለጠ: **(jokes)** እእእ!

**20.** ዳንኤል: እስኪ ይሄ ልቅ አፍህን ዝጋ፤ ብቻዬን ላንብብበት!

**21. SFX: PAPER RUSTLE AS በለጠ SNATCHES LETTER**

**22.** ዳንኤል: ስማ በለጠ። አቦ ደስ አይልም። ደብዳቤውን መልስልኝ። ሚስጥር ነው።

**23.** በለጠ: አልሰጥም! ኧረ የሚያስደንቅ ነገር አለው። እኔ አነብልሀለሁ! **(reads, imitates a girl’s voice)** “የኔ ውድ ዳኒ፤ ስለአንተ ከሰማሁ ጊዜያት ተቆጠሩ። ለፃፍኩልህ ኢሜሎች ምንም አይነት ምላሽ አልሰጠኸኝምም። ደህና ስለመሆንህም ይሁን ያኔ የገባህልኝን ቃል አሁንም ስለማክበርህ አላውቅም። …”

***KW BEGIN***

**24.** ዳንኤል: አቁም በለጠ! ነግሬሀለሁ። ደብዳቤውን መልስልኝ!

**25. SFX: COMMOTION AND PAPER RUSTLE AS ዳንኤል TRIES TO GET**

**THE LETTER BACK**

**26. በለጠ:** **(laughs)** ምናልባት በቅርጫት ኳስ ጨዋታ ታሸንፈኝ ይሆናል። ግን ይህንን ታግለህ አታሸንፍም እሺ። ደብዳቤው እንዴት እንደሚቀጥል ማወቅ አትፈልግም?

**27. ዳንኤል:** እሱ ያንተ ጉዳይ አይደለም።

***KW END***

**28. በለጠ:** **(continues reading)** “ምንም እንኳን ከኔ ርቀህ ብትገኝም አሁንም አፈቅርሀለሁ። ምን ያህል እንደማፈቅርህ የምገልፅበት አንድ አስደናቂ ነገር እያዘጋጀሁልህ ነው። ያንተው አፍቃሪ ፣አልማዝ” **(normal voice)** እእእ...

**29. ዳንኤል:** በቃ አፍህን ዝጋ፤ ምን ይሄ።

**30. MUSICAL INTERLUDE**

## <u>SCENE 2: AT THE POLICE STATION</u>

**31. SFX: ATMO INSIDE CELL AT POLICE STATION**

**32. SFX: INMATES CHAT IN LOW VOICES WHILE EATING**

**33. ፖሊስ ሙሉጌታ:** **(heard at a distance, speaking to** አቶ መኩሪያ**)** እሺ. የተከበሩ የምክር ቤት አባል አቶ መኩሪያ፤ እንግዲህ በፖሊስ ጣቢያችን ሙላቱ እና ቢጤዎቹ የተቀፈደዱት እዚህ ነው። መግባት ትችላለህ፤ እኔ እዚህ እቆያለሁ።

**34. SFX: FOOTSTEPS: አቶ መኩሪያ APPROACHES**

**35.** አቶ መኩሪያ: አመሰግናለሁ። መርማሪ።

**36.** አቶ ሙላቱ: እንዴ እንዴ ጭራሽ እዚህ ድረስ! እሺ የምክር ቤት አባል ። እንደምን አለህ አቶ መኩሪያ? ዘና በል እንግዲህ። ምነው አንተንም አሰሩህ እንዴ?

***KW BEGIN***

**37.** አቶ መኩሪያ: **(chuckles)**

**38.** አቶ ሙላቱ: ይቅርታ ስርዓት ለጎደለው አነጋገሬ። ለምሳ ምን ይምጣ? የጎድን ጥብስ? የወይን ጠጅ? አአአ! እረስቼው— ለካ ፖሊስ ጣቢያ ነው ያለነው። በዚህ እስር ቤት እንደለመድከው አይነት የተራቀቀ ምግብ የላቸውም። ግን— በዛ ፋንታ ይኼውልህ የተቀቀለ ጎመኔን ልሰጥህ እችላለሁ።

**39. INMATES: LAUGH**

**40.** አቶ መኩሪያ: **(in a low voice)** ወየውልህ አቶ ሙላቱ! አትገፋፋኝ።

**41.** አቶ ሙላቱ: አቶ መኩሪያ እዚህ እንዴ ከገባህ ውጪ ያለህ ገንዘብ ትርጉመቢስ ነው። እዚህ ሁላችንም አንድ ነን። ወንጀለኞች!

**42.** አቶ መኩሪያ: ገንዘብ ያለው ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሲጀመር የምታውቅ አይመስለኝም? በቂ ገንዘብ ካለህ ማንኛውንም ነገር መግዛት ትችላለህ።

**43.** አቶ ሙላቱ: **(still self confident)** እ! እውነትህን ነው? ታድያ እንደዛ ከሆነ እስካሁን እስር ቤት ውስጥ ምን ታደርጋለህ?

***KW END***

44. **አቶ መኩሪያ:** **(laughs calmly)** ምንአልባት ግልፅ ካልሆነልህ እኔን ካንተ የሚለየኝ ነፃ ሰው መሆኔ ነው። ወደዚህ የመጣሁት አችን ትንሽዬ ክፍል እና በጣም የጠነዛ ጎመንህን ካንተ ጋ ልቋደስ አይደለም። የመጣሁት ላስጠነቅቅህ ነው። ዘለፋህን ተው! ላልሰራኸው ወንጀል ለምን ታሰርኩ ብለህ እንኳን አትጠይቅም?

45. **አቶ ሙላቱ:** ስለምንድን ነው የምታወራው?

46. **አቶ መኩሪያ:** ስለ ስርቆት ወንጀሉ ነው የማወራው አቶ ሙላቱ። የጃለታን ቤት ዘረፋ እኔ ነኝ ያመቻቸሁት። ከዛም ከዚህ ተጠያቂው አንተ እንድትሆን አደረኩ።

47. **አቶ ሙላቱ:** **(shocked)** ምን?!እና እናንተ ነበራቹህ ማለት ነው?

48. **አቶ መኩሪያ:** **(low voice, menacingly)** አሸሸ! ድምፅህን ብትቀንስ ይሻልሀል ወይንስ እዚህ ያሉት አዲስ ጓደኞችህ ስለኛ ምስጢር እንዲሰሙ ትፈልጋለህ? ከመንገዴ ላይ ዞር እንድትልልኝ ስል ነው እዚህ ወህኒ ቤት ያስወረወርኩህ። አሁን በሰለም ከባለቤቴ እና ከልጃችን ጋ መኖር እንችላለን። ለኛ ሰላማዊ ኑሮ እንቅፋት ሆነህ ነበር። የምልህ ይገባህ ከሆነ...

**(calmly but threateningly)** ይህንን ጨዋታችሁን የማታቆሙ ከሆነ ሌላም ምን ማድረግ እንደምችል አስበው – በተለይ ደግሞ ባለቤትህ ላይ!– ልጅህን ስትሸጥልኝ ሙሉ ክፍያውን ሰጥቼህለሁ።

49. **አቶ ሙላቱ:** አቶ መኩሪያ ይህን ልታደርግ አትችልም--

50. **አቶ መኩሪያ:** **(cuts in)** ባትረብሸን ጥሩ ነውአቶ  ሙላቱ፤ ካለበለዚያ መገመት ከምትችለው በላይ ስቃይህን አበዛልሀለሁ።

51. **MNENE:** **(calls from far)** አቶ መኩሪያ ይከተሉኝ። የጉብኝት ጊዜዎ አልቋል።

**52.** አቶ መኩሪያ: እንግዲህ እንተያያለን። አቶ ሙላቱ! ባለቤትህን ከቤቴ ራቅ በይ ስትል ንገራት። መኖሪያ ቤቴ ድረስ እየመጣች አጮልቃ መመልከቷን አልተወችም። ለዛውም ሙሉ በሙሉ የእኔ የሆነችውን ልጅ! እየተደበቅኩ እመለከታለሁ ማለቷን ከቀጠለች ውሻዬ ሣልሳዊ እንዲሁ ዝም ብሎ የሚተዋት አይምሰልህ።

**53.** አቶ ሙላቱ: **(to himself)** ወይኔ ሰውዬው! እርጉም!

**54. MUSICAL INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: AT BONGO ACADEMY</u>**

**55. SFX: BONGO ACADEMY CLASSROOM, STUDENTS MAKING NOISE**

**56. SFX: HIGH-HEELED FOOTSTEPS APPROACHING**

**57. SFX: DOOR CLOSES LOUDLY**

**58.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(trying to control her anger)** ፀጥታ!

**59. CLASS: (immediately falls silent)**

**60.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የራሱ የሆነ ማንኛውም ተማሪ ሊያከብረውና ሊገዛበት የሚገባ ህግጋት አለው! ህጎቹ እናንተን ለመቅጣት ታስበው ሳይሆን ለናንተው ጥቅም ሲባል ነው።ግን አሁንም ቢሆን ደግሜ ደጋግሜ የምነግራችሁ ህጉን የማያከብር ዋጋውን እንደሚከፍል ነው። አንዳንዴ ይህን ስል ድንጋይ ላይ ውሃ ማፍሰስ ስለሚሆንብኝ በጣም አዝናለሁ። አንዳንዶቻችሁ ጨርሶ የምትባሉትን አትቀበሉም። አሁን የምጠራችሁ ተማሪዎች ወደዚህ ኑ!። ንጉሴ ጃለታ!

61. **SFX: CHAIR SCRAPING**

62. **SFX: FOOTSTEPS AS ንጉሴ STEPS FORWARD**

63. **CLASS:** **(murmurs)**

64. ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ዳንኤል ካሳሁን!

65. **SFX: CHAIR SCRAPES**

66. **SFX: FOOTSTEPS AS ዳንኤል STEPS FORWARD**

67. **CLASS:** **(more murmurs)**

68. ርዕሰ መምህርት ሰብለ: Silence! **(calls)** ምህረት ሙላቱ!

69. **CLASS:** **(even more noise)**

70. ርዕሰ መምህርት ሰብለ: **(to herself)** ሌላ ማን ቀረኝ --

71. **SFX: DOOR OPENS AND CLOSES**

72. **SFX: FOOTSTEPS ምህረት**

73. ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ምህረት አሁን ትምህርት ቤት መምጫሽ ሰዓት ነው? የትምህርት ክፍለ ጊዜው ተገባደ ል እኮ።

74. ምህረት: **(panting)** ይቅርታ ርዕሰ መምህርት ሰብለ። ታናሽ ወንድሜን ሆስፒታል መውሰድ ነበረብኝ።

75. እየሩስ: **(shouts)** ኦ ኦ! የደሀ ሰፈሯ ልጅ ተናገረች!

76. **CLASS:** **(laughs)**

**77. ርዕሰ መምህርት ሰብለ:** እየሩስ አፍሽን ካልዘጋሽ ስምሽን ቀጥዬ የምጠራው ተማሪ ትሆኛለሽ **(to the culprits)** ምህረት፣ ዳንኤል እና ንጉሴ:ዕስታችሁም አሁንኑ ወደ ቢሮዬ ኑ ተከተሉኝ! **(to the class)** የተቀራችሁት መፅሀፋችሁን ክፈቱና ገፅ 145 ላይ ያለውን መልመጃ ስሩ። እስክመለስ ድረስ እያንዳንዳችሁ ፀጥ ብላቹህ ስሩ።

**78. SFX: FOOTSTEPS** ርዕሰ መምህርት ሰብለ **AND THREE STUDENTS LEAVE**

**79. SFX: DOOR OPENS AND CLOSES**

**80. CLASS:** **(breaks into speculative noise)** ምን አድርገው ነው? … ዳንኤል አምልጦ ሊወጣ ነበር ሲባል ሰምቻለሁ… እውነት? ወዘተ **(fade out)**

**81. MUSICAL INTERLUDE**

**OR FADE FROM CLASSROOM TO OFFICE ATMO**

## SCENE 4: IN THE PRINCIPAL'S OFFICE

**82. ATMO:** ርዕሰ መምህርት ሰብለ**'S OFFICE ATMO (DURING CLASS)**

**83.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ጥሩ! አሁን እዚህ ለምን እንደጠራኋችሁ ታውቃላችሁ?

**84.** ምህረት/ዳንኤል/ንጉሴ: እናውቅም ርዕሰ መምህርት ሰብለ!

**85.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: መልካም ከንጉሴ እንጀምር **(sarcastic)** ንጉሴ ጃለታ የቦንጎ አካዳሚ የእፅ ጌታ እንደሆነ ግልፅ ነው። ማሪዋና ብቻ አይደለም የሚያጨሰው አልኮል መጠጥም ይጠጣል። የምትለው ነገር አለ ንጉሴ?

**86.** ንጉሴ: **(timidly)** የለም መምህርት!

**87.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ይኼውና ደግሞ ዳንኤል ካሳሁን። የታዋቂው ካሳሁን ድርጅት ወራሽ በቦንጎ ት/ቤት ደግሞ የብዙ ልጃገረዶች ልብ ማራኪ! በቅርቡ ዳንኤል እና ምህረት ባልና ሚስት ሆነው ተስተውለዋል። አሁን ይሄው የመጀመሪያ ልጃቸውን እየጠበቁ ነው። አይደለም እንዴ ዳንኤል?

**88.** ዳንኤል: **(silence)**

**89.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ምህረት?

**90.** ምህረት: **(silence)**

**91.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ያው እንግዲህ ሰው የዘራውን ያጭዳል አይደል የሚሉት። ሶስታችሁም ከቦንጎ አካዳሚ ታግዳችኋል። «ህጉን ያላከበረ ዋጋውን ይከፍላል» አሁን ሁላችሁም እቃችሁን ሰብስቡና ት/ቤትን ለቃችሁ ሂዱ። የቦርዱ አባላት የሚወስኑትን ስንሰማ እናሳውቃችኋለን።

## 92. ALL THREE STUDENTS REACT AT SAME TIME

**93.** ዳንኤል: ግን... እኔ ምንም--

**94.** ንጉሴ: እባክዎ --

**95.** ምህረት: **(Cries)** ይቅርታ ያርጉልኝ...

**96.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ምንም አይነት ግን ፣ ምንም አይነት ልመናም ሆነ ምክንያት አልቀበለም። በእናንተ በጣም ነው ያዘንኩት። በሁላችሁም!

## 97. OUTRO – NARRATOR:

**እኛም የዛሬውን «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» የተሰኘውን የበማድመጥ መማር ተከታታይ የሬዲዮ ድራማ በዚሁ እናጠናቅቃለን። ንጉሴ፣ ዳንኤል እና ምህረት ይህንን ዜና እንዴት ይቀበሉት ይሆን? ርዕሰ መምህርቷ ሁሉንም ከትምህርት ቤት ማባረራቸው ተገቢ ነው ትላላችሁ? ስለዚህ በፌስቡክ ገፃችን ላይ ተወያዩበት። ይህንን እና ሌሎች ክፍሎችን ደግማችሁ መስማት ከፈለጋችሁ dw.de/lbe ድረ ገፅን ጎብኙ። በእውነተኛው ዓለም ስለሚፈፀመው ዜና ለመስማት ደግሞ dw.de/Amharic ገፅን መጎብኘት ትችላላችሁ። ለዛሬው በእዚሁ እንሰናበት፤ ደህና ሁኑ!**